# የኢ.ህ.ባ.ሴ.ማ በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶችን አስመልክቶ ያደረገዉ ምልከታ

## በቅድመ-ምርጫ እና ምርጫ ወቅት የተደረጉ ምልከታዎች ግኝት መግለጫ

የኢትዮጵያ ህግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር
ስ.ቁ: - 0115 50 87 83
ኢሜል:- info@ewla-et.org /ewla1995@gmail.com
ዌብሳይት:- WWW.ewla-et.org

# መቅድም

የኢትዮጵያ ህግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር የ2013 ዓ.ም 6ኛዉ ሃገር-ዓቀፍ ምርጫ አካታችነትንና በተለይም በሴቶች ሙሉ እና እኩል ተሳትፎ ዙሪያ አስተዋፅኦ ለማበርከት በቅድመ-ምርጫ ወቅት እና በምርጫ ቀን በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶችን በሚመለከት ምልከታ (የመታዘብ ስራ) አከናዉኗል:: ምልከታዉ ሴት መራጮች ፣ ታዛቢዎች ፣ የምርጫ ጣቢያ ሰራተኞች ፣ እጩ ተመራጮች እና የምርጫ ጣቢያ ታዛቢዎች በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ በሚፈፀሙ ጥቃቶች የተነሳ እንዴት ተፅዕኖ እንደደረሰባቸዉ ምልከታ አድርጓል:: የምልከታ ግኝቶችና የመፍትሄ ሃሳቦች አላማ ባጠቃላይ በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ በሚፈፀሙ ጥቃቶች ዙሪያ በሁሉም ማህበረሰብ ዘንድ ግንዛቤ እንዲስፋፋ እና በባለድርሻ አካላት ዘንድ በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ ሊፈፀሙ ስለሚችሉ ጥቃቶች ግንዛቤ በማስፋፋት ወደፊት በሚደረጉ ምርጫዎች ለሴቶች ምቹ ሁኔታን መፍጠር ነዉ::

ማህበሩ 150 የቅድመ-ምርጫ ሂደቶችን የሚታዘቡ የረዥም ጊዜ ታዛቢዎችን እና 130 የድምፅ መስጫ (የምርጫ)ቀንን የሚታዘቡ ታዛቢዎችን ቀጥሮ ስልጠና ሰጥቷል:: የታዛቢዎች የረዥም ጊዜ ምልከታ ለመጀመር ግን ምርጫ ቦርድ ለታዛቢዎች የሚሰጠዉ የዕዉቅና ፈቃድ (ባጅ) በመዘግየቱ እና በአንዳንድ የሃገሪቱ ክፍሎች የነበረዉ የፀጥታ ሁኔታ ታዛቢዎች በነፃነት እንዲንቀሳቀሱና የምልከታ ስራቸዉን በታቀደለት መሰረት እንዲጀምሩ የሚያስችል ባለመሆኑ የተነሳ የመታዘብ ስራችን ላይ ገደብ አሳድሯል:: በብዙ ሃገራት ማህበረሰቦች ዘንድ በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶች እየተለመዱ መጥተዋል:: ከዚህ የተነሳም ከምርጫ ጋር ተያይዘዉ የሚፈፀሙትን ጨምሮ በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ የሃይል እርምጃዎችን መመዝገብ እና ማመልከት ቀላል አይደለም:: ከዚህ በታች የተቀመጡት የምልከታ ግኝቶች በ2013 ዓ.ም በኢትዮጵያ በተካሄደዉ ሃገር ዓቀፍ ምርጫ ከተከሰቱ በሴቶች ላይ የተፈፀሙ ጥቃቶች መካከል የኢ.ህ.ባ.ሴ.ማ ያሰማራቸዉ ታዛቢዎች በተገደበ የምልከታ ጊዜ ዉስጥ የተመለከቷቸዉ ወይም የሰሟዋቸዉ እና ወደ ማህበሩ ዋናዉ ቢሮ የመረጃ መሰብሰቢያ ቋት ማዕከል ልከዋቸዉ የመጣራት ሂደት የተደረገባቸዉ ናቸዉ::

ቅድመ-ምርጫ ሂደቶች ላይ ምልከታ ያደረጉ የረዥም ጊዜ ታዛቢዎች 341 መጠይቆችን ሞልተዉ በማጠናቀቅ ያቀረቡ ሲሆን በሴቶች ሙሉ እና ዉጤታማ ተሳትፎ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያስከትሉ የቻሉ ጥቃቶችን በተመለከቱበት እና በሰሙበት ወቅት ሞልተዉ ያጠናቀቋቸዉን 100 የወሳኝ ክስተቶችን ግኝቶች በወሳኝ ክስተቶች መሙያ መጠይቅ ላይ ሞልተዉ መላክ ችለዋል:: ከነዚህ በኢ.ህ.ባ.ሴ.ማ ታዛቢዎች በቅድመ-ምርጫ ወቅት ከተመዘገቡት ክስተቶች መካከል በሴቶች ላይ የተፈፀመ ዛቻ እና ማስፈራራት በስፋት የታየ እና የተመዘገበ የጥቃት አይነት (4) ነበር ::

በተጨማሪም የኢ.ህ.ባ.ሴ.ማ ታዛቢዎች 7 የወሲባዊ ትንኮሳ ድርጊቶችን ፤ 2 አካላዊ ጥቃቶችን እና 2 በፀጥታ አስከባሪ አካለት የተፈፀመ የሴት ዕጩ ተወዳደሪዎችን የምረጡኝ ዘመቻ ያስተጓጎሉ ድርጊቶችን መታዘብ ችለዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ሴት መራጮች በመራጮች ትምህርት ወይም በምርጫ ዘመቻዎች እንዳይሳተፉ እና ለመሳተፍ ተስፋ እንዲቆርጡ የተደረጉ (8) ድርጊቶች ተመዝግበዋል፡፡ እንዲሁም ሴተች በምረጡኝ ዘመቻዎች እንዳይካተቱ የሚያደርግ (8) ክስተቶች ተመዝግበዉ ነበር፡ ፡ የኢ.ህ.ባ.ሴ.ማ ታዛቢዎች የፖለቲካ ፓርቲ አባላት እና የአካባቢ አስተዳደር ባለስልጣናት ሴቶችን በማባበል ድምፅ እንዲሰጧቸዉ የተሞከሩ 10 ክስተቶችን ሪፖርት አድርገዋል፡፡ የኢ.ህ.ባ.ሴ.ማ ታዛቢዎች በተጨማሪም የቅድመ-ምርጫ ሂደቶች አካታችነትንና የሴቶች ፖለቲካዊ ተሳትፎን ሁኔታ ገምግመዋል፡፡ ታዛቢዎቹ 39 አካል ጉዳተኞች ወደ ምርጫ ጣቢያ ለመግባት አስቸጋሪ የነበሩ እና በምርጫ አስፈፃሚዎች የተፈፀባቸዉን ያልተገባ አያያዝ ታዝበዋል ወይም አቤቱታዎችን ሰምተዋል፡፡

የኢትዮጵያ ህግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር በድምፅ መስጫ ቀን የድምፅ አሰጣጥ ሂደቶችን እና በምርጫዉ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶችን ለመታዘብ 369 የምርጫ ጣቢያዎችን መነብኘት የቻሉ 130 ታዛቢዎችን አሰማርቶ ነበር፡፡ ሁሉም የተሰማሩት ታዛቢዎች የምርጫ ቀን መጠይቆችን አጠናቀዉ የሞሉ ሲሆን 100 የወሳኝ ክስተቶች መሞያ መጠይቆችንም አጠናቀዉ በመሙላት ማስመዝገብ ችለዋል፡፡ ምልከታ ከተደረገባቸዉ የምርጫ ጣቢያዎች 80% ሚሆኑት ላይ ሰልፎች የተስተዋሉ ሲሆን 58% በሚሆኑት ላይ ደግሞ ለወንዶች እና ሴቶች የተለዩ የሰልፍ መስመሮች ባለመኖራቸዉ በሴቶች ላይ ሊፈፀም የሚችል የፆታዊ ትንኮሳ ስጋትን ከፍ ሊያደርገዉ ችሏል፡፡

በኢ.ህ.ባ.ሴ.ማ ታዛቢዎች ምልከታ የተደረገባቸዉ አንዳንድ የምርጫ መታዘብ ግኝቶች የተመዘገቡት ተሰልፈዉ በነበሩ ሴት መራጮች ላይ የተፈፀሙትን ወሲባዊ ትንኮሳዎች ያከትታሉ፡፡ በኢ.ህ.ባ.ሴ.ማ ታዛቢዎች ምልከታ በተደረገባቸዉ ጣቢያዎችዉስጥ የሴቶች ዉክልና አናሳ የነበረ ሲሆን ከምርጫ ጣቢያዎቹ 83% ወንድ ሊቀመንበሮች የነበራቸዉ ሲሆን 18% ብቻ በሚሆኑት ሴት ሊቀመንበሮችን አስተዉለዋል፡፡

የማህበሩ ታዛቢዎች በምርጫዉ ቀን በሴቶች ላይ የተፈፀሙ 13 ጥቃቶችን የመዘገቡ ሲሆን ከነዚህ መካከል አካላዊ ጥቃት (2) ፤ ወሲባዊ ትንኮሳ (11) እንዲሁም ስነ-ልቦናዊ ጥቃት (2) ተመዝግበዋል፡፡ የድምፅ መስጫ ካርዶች እጥረት ያጋጠማቸዉ ጣቢያዎችም በድምፅ መስጫ ቀኑ የኢ.ህ.ባ.ሴ.ማ ታዛቢዎች ከመዘገቧቸዉ (17ቱ) እጅግ በጣም አሳሳቢ ከሚባሉት ክስተቶች መካከል የሚመደቡ ነበሩ፡፡

ኢ.ህ.ባ.ሴ.ማ ታዛቢዎች በተጨማሪም እገዛ የሚያስፈልጋቸዉ የማይመስሉ ሴት መራጮች በምርጫ አስፈፃሚ አካላት እገዛ እንደተደረገላቸዉ ምልከታ አድርገዋል፡፡ እንዲሁም (3) ለመምረጥ መስፈርቱን ያላሟሉወንዶች እና (2) ለመምረጥ መስፈርቱን ያላሟሉ ሴቶች ድምፅ እንዲሰጡ እንደተፈቀደላቸዉ ታዝበዋል፡፡ በምርጫ ጣቢያዎች መገኘት ያልተፈቀደላቸዉ (5) ግለሰቦች በጣቢያዎች እንደተገኙ ፤ በ(3) የምርጫ ጣቢያዎች እንደተሰረዘ እና (4) ምርጫዉን የመታዘብ ስራን እንዳያከናዉን የታዛቢዎች መብት እንደተነፈገ ታዝበዋል፡፡ አንድ የኢ.ህ.ባ.ሴ.ማ ታዛቢ ደግሞ ቆጠራ እስኪጠናቀቅ በሚል ያለፈቃዱ ያለምግብ እና ዉሃ ሌሊቱን እንዲያሳልፍ እና እስከሚቀጥለዉ ቀን ድረስ እንዲቆይ ተደርጓል፡፡

የኢትዮጵያ ህግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር በቅድመ ምርጫ እና በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የተፈፀሙ የሃይል እርምጃዎችን (ጥቃቶችን) በሚመለከት ባደረገዉ ምልከታ ያገኛቸዉን ግኝቶች እና የመፍትሔ ሀሳቦች ያካተተ ሪፖርት የድህረ-ምርጫ ሂደቶችም በተጠናቀቁ ጊዜ የሚያቀርብ ይሆናል፡፡

## ምክረ-ሃሳቦች

ከላይ በቀረቡት ግኝቶች መሰረት ማህበሩ የሚከተሉትን የመጀመሪያ ደረጃ የመፍትሄ ሀሳቦችን ቁልፍ የሆኑ ባለድርሻ አካላት ላይ በማተኮር ይሰጣል።

### ለኢትዮጲያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ

- በኢትዮጲያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ውስጥም ሆነ ውጪ የትኛዉም ዓይነት በሴቶች ላይ የሚፈጸም ጥቃትን መከልከልን ጨምሮ ጥቃቶች ሲፈጸሙ የሚከተሉ ቅጣቶችን ማብራራት፣ ሚስጥር በጠበቀ ሁኔታ የሪፖርት ማድረጊያ ሰንሰለቶችን መፍጠርና ይህን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች እንዲፈጸሙ ማስደረግ
- ወሲባዊ ይዘት ያላቸውን ክብት የሚነኩ የሆኑ የቋንቋ አጠቃቀሞችን በሴት እጬዎች፣ ድምጽ ሰጪዎች ፣ ታዛቢዎች፣ የምርጫ ጣቢያ ሰራተኞችና የተመረጡ ሴቶች ላይ እንዳይፈፀሙ  የሚከለክሉ ህጎች\ድንጋጌዎች መተግበራቸውን ማረጋገጥ
- በኢትዮጲያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ፖለቲካ ፓርቲዎች አስገዳጅ የሆነ የስነ-ጾታ ምጥጥን እንዲኖርና መመረጥ ያለባቸውን የሴት አባላት ዝቅተኛ ቁጥር እንዲኖር ያለውን ቁርጠኝነት እንዲፈጽም ማስገደድ
- የኢትዮጲያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የስነ-ጾታ ክፍል ሚናዎቹንና ሀላፊነቶቹን ለመወጣት የሚያስችል አቅምና ስልጣን ያለው መሆኑን ማረጋገጥ
- የምርጫ አስፈጻሚዎችንና የጣቢያ የጸጥታ አካላትን ስለ ስነ-ጾታ እኩልነት፣ በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን ለመቀነስ የሚያስችሉ አሰራሮችን ማስቀመጥ።
- በመራጮች ትምህርት ውስጥ የምርጫ ካርድ ሚስጥራዊነት አስፈላጊነትን በመመልከት ንቃት ህሊና ከፍ ማድረግን ጨምሮ በምርጫ ውቅት በሴቶች ላይ ስለሚፈጸሙ ጥቃቶች ጽንሰ ሃሳብን ማካተት
- የኢትዮጲያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በምርጫ ሂደት የሴቶችን እኩልነትና ተሳትፎ ከፍ ለማድረግ ላለው ቁርጠኝነት መወሰድ ስላለባቸው ግልጽ እርምጃዎች ንቃተ ህሊናን ከፍ ማድረግ
- ለኢትዮጲያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሰራተኞች ፣ አባላትና ባለድርሻ አካላት በምርጫ ሂደት ወቅት በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶች በሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ ስለሚያሳድሩት ተጽእኖ እና የምርጫን ዲሞክራሲያዊ ሂደት ጥራት በማሳነሱ አሰራራቸች ላይ ለስነ-ጾታ ጉዳዮች ጥንቃቄ የማድረግ ስልጠናን መተግበር
- ከምርጫ በፊት ተንቅሳቃሽ የምዝገባ ቡድንን ሴቶችን ያካተተ በማሰማራት በተለይም በገጠር አካባቢዎች የመራጭ ሴቶችን ምዝገባ የማሳለጥ ስራ ማከናውን
- ለታዛቢዎች የእዉቅና ፈቃድ (ባጅ) በጊዜ እንዲሰጥ ማድረግና በምርጫ የጊዜ ሰሌዳ ላይ የሚደረጉ ለዉጦችን ለህዝቡ በጊዜ ማሳወቅ፡፡

### ለኢትዮጵያ መንግስት

- በምርጫ ሂደት ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶችን በመመርመር እና በዳኝነት ስራ ላይ ለተሰማሩ ህግ አስፈፃሚ አካላት ፣  ለፖሊስ ፣ ለህግ አስከባሪ አካላት ስነ-ፆታ ተኮር የሆነ ስልጠናን እንዲያገኙ ማድረግ
- ሴት የምርጫ አስፈፃሚ/አስተባባሪ ሰራተኞችን ደህንነት ለመጠበቅ ይረዳ ዘንድ የሴት ፀጥታ አስከባሪ አካላትን ቁጥር ከፍ ማድረግ
- በሴቶች ላይ ሚፈፀሙ ወሲባዊ ትንኮሳዎችን ለመከላከል የሚያስችሉ የህግ ለዉጦችን ማድረግ

- ህግ አስከባሪ አካላት በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ የጥቃት ወንጀሎችን በህግ ፊት ለማቅረብ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጋር በመተባበር በቅርበት እንዲሰሩ ማበረታታት፡፡

## ለሲቪክ ማህበራት ድርጅቶች

- ከተመረጡ አሰራሮች ጋር በተጣጣመ መልኩ ስነ-ፆታ ተኮር የሆኑ እና ለስነ-ፆታዊ ጉዳዮች ምላሽ የሚሰጥ የምርጫ መታዘብ ስራዎችን ማከናወን እንዲቀጥሉ
- የሴቶችን ፖለቲካዊ ተሳትፎ ሚና የሚያሳዩ እና በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶችን አስመልክቶ ግንዛቤ የማስፋፋት ዘመቻዎችን እንዲደግፉ
- በምርጫ ሂደቶች ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶችን ለመቀነስ ይረዳ ዘንድ ምርጫ አስፈፃሚዎችን (ሰራተኞችን) ፤ ፖሊስ ፤ ህግ አስከባሪ እና አስፈፃሚ አካላትን ማሰልጠን
- በምርጫ ሂደቶች በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ የሃይል እርምጃዎችን ለመታገል በሴት አመራሮች መካከል የአንድነት ትስስሮችን ማሳደግ የሚያስችሉ መድረኮችን መፍጠር
- ሴቶች በምርጫ ሂደቶች ሙሉ በሙሉ እና በእኩልነት ለመሳተፍ የሚያስችላቸዉን ህጎችና ፖሊሲዎች ለማሻሻል ያለሙ የሙግታ/ግፊት የመፍጠር ስራዎችን መስራት

## ለፖለቲካ ፓርቲዎች

- የሴቶች በብት እንዲከበር የሚያስችሉ የስነ-ምግባር ህጎችንና የድርጊት መርሃ-ግብሮችን ማጎልበት እና ማስፈፀም ፤ እንዲሁም ወሲባዊ ጥቃቶችን መቅረፍ የሚያስችሉ የማይታገሱ ፖሊሲዎችን ማዉጣት
- ለፖለቲካ ፓርቲ አባላትና ለፓርቲ የምርጫ ታዛቢዎች የግድ ሊወስዱት የሚገባቸዉን የስነ-ፆታ ስልጠናና ትምህርቶችን መስጠት
- ስለ ስነ-ፆታ እኩልነትና በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ ስለሚፈፀሙ ጥቃቶች የፓርቲ የዉስጥ መተዳደሪያ ደንብና አሰራሮችን መቆጣጠር እና ማስፈፀም
- የተመረጡት ሴት ባለሥልጣናትን ቁጥር የሚያስገድድ አስገዳጅ የሥርዓተ-ፆታ ኮታ እንዲቀበሉ
- መመረጥ ያለባቸዉን የሴት ተመራጮች ዝቅተኛ ቁጥር በሚመለከት አስገዳጅ የሆነ የስርዓተ-ፆታ ኮታዎች መተግበር

## ለመገናኛ ብዙሃን (ሚዲያዎች)

- የስርዓተ-ፆታ እኩልነት አለመኖርና ስነ-ፆታን በሚመለከት ያሉ የተሳሳቱ አመለካከቶች (አድሎአዊነትን) በሚመለከት በሚያቀርቡት የዘገባ ይዘት ትምህርትን መስጠት
- በስነ-ፆታ እኩልነትና በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ ስለሚፈፀሙ ጥቃቶች ለሚዲያ ሰራተኞች የአቅም ግንባታ ስራን ማከናወን
- በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ ስለሚፈፀሙ ጥቃቶች በተለያየ መልኩ ማዉራት የሚያስችሉ መድረኮችን በመፍጠር የግንዛቤ ማስፋፊያ ስራዎችን መስራት
- ስለ ምርጫ ሂደቶች የሴቶችን ንቃተ ህሊናና መረዳት ከፍ ለማድረግ የሚያስችሉ መረጃዎችን በሚገባ መልኩ ማዘጋጀት እና ማሰራጨት

## ለአጋር ድርጅቶች (ለጋሽ ተቋማት)

- በመንግስት ፤ በምርጫ ቦርድ እና የሲቪክ ማህበራት አነሳሽነት በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ በሚፈፀሙ ጥቃቶች ዙሪያ ግንዛቤ ለመፍጠር የሚጀመሩ እንቅስቃሴዎችን መደገፍ
- በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ በሚፈፀሙ ጥቃቶች እና በፆታዊ እኩልነት ዙሪያ የባለድርሻ አካላትን አቅም ለማጎልበት እገዛ ማድረግ
- በፆታ ተኮር እና ስነ-ፆታዊ ምልከታዎች ላይ የሃገር በቀል የሲቪክ ማህበራት ድርጅቶችን ጥረት መደገፍ

# መግቢያ

በ2013 ዓ.ም 6ኛ ዙር የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ላይ የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ እንደገለጸው ከሆነ ድምር የተመዘገቡ ድምጽ ሰጪዎች ብዛት 38,234.9101 ነው፡፡ በ2013 ዓ.ም ለተከናወነው ለዚህ አካታች የምርጫ ሂደት አስተዋጾ ለማድረግ በተለይም የሴቶችን ሙሉ እና እኩል ተሳትፎ ለማረጋገጥ የኢትዮጵያ የህግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር በቅድመ ምርጫ እና በምርጫ ቀን በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸም ጥቃቶች ላይ ምልከታ አድርጓል፡፡

በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸም ጥቃት በ6ኛው ዙር የኢትዮጵያ ምርጫ ወቅት በብዙ ምክንያቶች ከወንዶች ጋር ሲነጻጸር ሴቶች ባላቸው የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ ለጉዳት ያለካቸዉን ተጋላጭነትን አስከትሏል፡፡

በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸም ጥቃት ድርጊቶች ከጥቃቱ በተረፉት እና በቤተሰቦቻቸው ላይ ብቻ ጉዳትን የሚያስከትል ሳይሆን ነገር ግን በሴቶች ላይ ጉልህ የሆነ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ኪሳራን ያስከትላል፡፡

በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸም ጥቃት ቁጥጥር/ክትትል አላማ በምርጫ ሂደት ወቅት ለሴት ድምጽ ሰጪዎች፣ ለሴት እጩዎች፣ ለሴት ምርጫ አስፈጻሚዎች፣ ለመገናኛ ብዙሃን ተቋማት እና ጋዜጠኞች እንዲሁም በአጠቃላይም ለዜጎች ደህንነቱ የተጠበቀ እና እኩል ተሳትፎ ያለበት አካባቢን ለመፍጠር አስተዋጾ ማድረግ ነው፡፡ በዚህ ምልከታ/ጥናት የተሰበሰቡ መረጃዎች ለወደፊቱ በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸም ጥቃት በሚመለከት ንቃተህሊናን ለመፍጠር እና በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚከናወን የምርጫ እና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ላይ የሴቶችን የላቀ ተሳትፎ ለማረጋገጥ ለሚደረግ አድቮኬሲ ስራ አስተዋጾ የሚያደርግ ነው፡፡

በ2013 ዓ.ም የተከናወነው የኢትዮጵያ አጠቃላይ ምርጫ በመጀመሪያ ሊከናወን ታቅዶ የነበረው በግንቦት 2012 ዓ.ም (ሜይ 2020 እ.ኤ.አ) ሲሆን በኮቪድ 19 ወረርሺኝ እና በጸጥታ መደፍረስ እንዲሁም በምርጫ አስተዳደር ዝግጅቶች የተነሳ ለተወሰኑ ጊዜያት ሲራዘም ከቆየ በኋላ በሰኔ 14/2013 ዓ.ም ተከናውኗል፡፡ የሰኔ 2013 ዓ.ም የድምጽ መስጫ ካርዶች ለፌደራል መንግስት እና ለክልል ምክርቤቶች/አስተዳደር ድምጽ ለመስጠት የታቀዱ ነበሩ፡፡ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የሰኔ 2013 ዓ.ም የመራጮች የጊዜ ሰሌዳ የሐረሪ ፣ የትግራይ እና የሶማሌ ክልሎችን ያላካተተ እና በኦሮሚያ ፣ አፋር ፣ ቤንሻንጉል-ጉሙዝ ፣ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት እና ሲዳማ እንዲሁም በአማራ ክልሎች ላይ የተወሰኑ አካባቢዎችን ያላካተተ ነበር፡፡

- አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር - 20/8/2013 ዓ.ም
- ጋምቤላ ክልል - ሚያዚያ 20 2013 ዓ.ም
- ቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል - ሚያዚያ 25 2013 ዓ.ም
- ሲዳማ ክልል - ሚያዚያ 26 2013 ዓ.ም

- ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልል - ግንቦት 04 2013 ዓ.ም
- ድሬ ዳዋ ከተማ አስተዳደር - ግንቦት 04 2013 ዓ.ም
- አማራ ክልል - ግንቦት 07 2013 ዓ.ም
- ኦሮሚያ ክልል - ግንቦት 14 2013 ዓ.ም

[1]The NEBE Official Facebook page accessed June 23

የኢትዮጵያ የህግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር በቅድመ-ምርጫ ያለን ሂደት የሚታዘቡ የረዥም ጊዜ ታዛቢዎች 341 መጠይቆችን በሙሉ አጠናቀዉ ሞልተዉ በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ ስለሚፈጸሙ ጥቃቶች ምልከታ አቅርበዋል፡፡ ታዛቢዎቹ በቅድመ ምርጫ ሂደት ወቅት በሴቶች ሙሉ እና ውጤታማ ተሳትፎ ላይ ተጽእኖ ሊያሳድሩ የሚችሉ ጥቃቶችን እንደተመለከቱ ወይም ስለእነርሱ እንደሰሙ 100 ወሳኝ የሆኑ ክስተቶች ቅጾችን ሞልተዋል፡፡ ስለ ጥቃት ፈፃሚዎች እና ከጥቃት ስለተረፉ ግለሰቦች አይነት መረጃ ለኢትዮጵያ ህግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር ዋና ጽ/ቤት የመረጃ ቋት ሪፖርት አድርገዋል፡፡

በተጨማሪም ሴቶችንና ሌሎች ተጎጂ የማህበረሰብ አካላትን በምርጫ ሂደት ውስጥ የማካተትን መሰረታዊ የሂኑ ጉዳዮችምም ገምግመዋል፡፡ የረጅም ግዜ ክትትል ስራው በምርጫ ሂደት ውሰጥ አካታችነትን የሚመለከት መሰረታዊ የሆኑ ጉዳዮችንም ገምግሟል፡፡

የረጅም ግዜ ምልከታዉ የኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ የዕውቅና መታወቂያ (ባጅ) አሰጣጥ ከመዘግየቱ እና ባንዳንድ የምርጫ ካባቢዎች ከነበረው የጸጥታ ችግር የተነሳ ታዛቢዎች በነጻነት ተዘዋውረው የክትትል ስራውን በመጀመሪያ በታቀደው መሰረት ለማከናወን ባለመቻላቸው ምክንያት የተገደበ ነበር፡፡ በሴቶች ላይ የሚፈጸም ጥቃት በብዙ ሀገሮች እና ማህበረሰቦች እየተለመደ መምጣቱን ቀጥሏል፡፡ በዚህ መሰረት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶች /ክስተቶች/ የመርጫ ጥቃቶችን ጨመሮ በቀላሉ ሊመዘገቡ እና ሪፖርት ሊደረጉ የሚችሉ አይደሉም፡፡

ከዚህ በታች የተገለጹት ግኝቶች በ2013 ዓ.ም ምርጫ የተከሰቱትን ከምርጫ ጋር በተያያዘ በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን የተወሰነ መጠን ብቻ የሚገልጹና የኢትዮጵያ የህግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር ታዛቢዎች ሊታዘቧቸው የቻሏቸውን ወይም የሰሟቸውን እና በክትትል የተገደበ ግዜ ውስጥ ለኢትዮጵያ የህግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር ዋና መስሪያ ቤት የመረጃ ቋት ሪፖርት ማድረግ የቻሏቸውን ብቻ የሚወክሉ ናቸው፡፡ በተመሳሳይ ግዜ የኢትዮጲያ ምርጫ ቦርድ በኢትዮጲያ የመራጮች ምዝገባ ቀነገደብን ለማራዘም መወሰኑን ለማህበሩ በአዲሰ አበባና በተወሰኑ የደቡብ ብሄር ብሀረሰቦች እና ህዘቦች ክለላዊ መንግስት ፣ በጋምቤላ እና ቤንሻንጉል ጉሙዝ የመራጮች ምዘገባ ሂደትን ለመታዘብ አስችሎታል፡፡ የኢትዮጵያ ህግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር በአዲሰ አበባ ሰኔ 12 ቀን 2013 ዓ.ም የመራጮቸ ምዘገባን በተመለከተ ስላገኛቸዉ ግኝቶች መግለጫ[2] ሰጥቶ ነበር፡፡

[2] EWLA Website ‹https://ewla-et.org/preliminary-observations-findings-on-voter-registration-process/ › accessed 23 June 2021.

## በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶችን አስመልክቶ የተደረገ የረጅም ጊዜ ምልከታ ግኝቶች

በረጅም ግዜ ክትትል ወቅት የኢትዮጵያ የህግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር ከምርጫ በፊት ያ ለውን ሂደት የሚታዘቡ ታዛቢዎች በቅድመ ምርጫ ወቅት የምርጫ ቅስቀሳውን ሁኔታ አካባቢ እና በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን ታዝበዋል፡፡ በተለይ እንዴት የሴት መራጮች፣ ታዛቢዎች የምርጫ ጣቢያ ሰራተኞች፣ ዕጩዎች እና የምርቻ ጣቢያ ታዛቢዎች በምርቻ ወቅት በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶች የተነሳ ተጽእኖ ሊደርስ እንደሚችል ገምግመዋል፡፡የክትትሉ ግኝቶች በምርቻ ወቅት በሴቶች ላ ሊደርሱ ስለሚችሉ ጥቃቶች በህዝቡ ዘንድ እና በምርጫ ባለድርሻ አካላት  ዘንድ ኝቃተ ህሊናን ለመፍጠር እና ለወደፊቱ ቢኖሩ ምርጫዎች ለሴቶች የተሻለ ሁኔታን ለመፍጠር አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡ ማህበሩ ታዛቢዎች በሴቶች ላይ የተፈጸሙ የዛቻ ወይም የማስፈራራት 41 ክስተቶች የታዘቡ ሲሆን ይህም የሴት መራጮችን (28)፣ ለመምረጥ የሚችሉ ሴቶችን (2) የፓርቲ  አባላትን (3) የሚያካትት ነው፡፡ጥቃት ፈጻሚዎች በአብዛኛው የፓርቲ አባላትን ወይም ደጋፊዎችን (15)፣ ድምጽ ለመስጠት የተመዘገቡ ግለሰቦችን (3)፣ ባል/ሚስት (6)፣ ሌላ የቤተሰብ አባላት (4) እና የጸጥታ አስከባሪ አካላትን ወይም ፖሊስ ያካተቱ ነበሩ፡፡

የአካባቢ አስተዳደር አካላት ጭምር የሴት መራጮችን እነርሱ በሚፈልጉት ሁኔታ ድምፅ እንዲሰጡ ጫና በመፍጠርና ከምርታማ የሴፍቲኔት ፕሮግራም እንሰርዛችኋለን በማለት ዛቻ ወይም ማስፈራራት ፈፅመዋል፡፡

የኢ.ህ.ባ.ሴ.ማ ታዛቢዎች እነዚህን በምርጫ ሂደት የተፈፀሙ የጥቃት ክስተቶችን የመዘገቡት በአብዘሃኛዉ ከአማራ ክክል ፣ ኦሮሚያ ክልል እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች ነዉ፡፡ የተወሰኑ ክስተቶች ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል እና ከአዲስ አበባ ከተማ አሰስተዳደር ጭምር ተመዝግበዋል፡፡

የኢ.ህ.ባ.ሴ.ማ ታዛቢዎች በሴት መራጮች ወይም ለመምረጥ በሚችሉ ሴቶች (3) ፣ ለመምረጥ በመመዝገብ ላይ በነበሩ ሴቶች (2) ፣ በፖለቲካ አባላት ወይም ደጋፊዎች (1) እና ሌሎችም (1) ላይ ወሲባዊ 7 ወሲባዊ ትንኮሳዎች ተመዝግበዋል፡፡

በ5ቱ ክስተቶች ትንኮሳዉ የተፈፀመዉ በቃል ሲሆን በሁለቱ ደግሞ አካላዊ ወይም ያልተፈለገ ንክኪ በፍጠር የተፈፀሙ ናቸዉ፡፡ ብዙዎቹ ወሲባዊ ትንኮሳዎች የተፈጠሩት በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ሲሆን ከጋምቤላ እና አማራ ክልል ከየአንዳንዳቸዉ አንድ ክስተት ተመዝግቧል፡፡

የኢ.ህ.ባ.ሴ.ማ ታዛቢዎች በሴት ምርጫ አስፈፃሚወፖች ላይ ስለደረሱ አካላዊ ጥቃቶች (2) ምልከታ አድርገዉ ነበር፡፡ ጥቃቱን ፈፃሚዎች ወንዶች እና ሴቶች የፖለቲካ ፓርቲ አባላት ሲሆኑ ሴት የምርጫ አስፈፃሚዎችን በጥፊ በመምታት እና በመደብደብ የተፈፀሙ ጥቃቶች ናቸዉ፡፡ ክስተቶቹ በቤንሻንጉል ክልል እና በድሬዳዋ ከታማ አስተዳደር የተመዘገቡ ናቸዉ፡፡

የኢ.ህ.ባ.ሴ.ማ ታዛቢዎች  ፀጥታ አስከባሪ አካላት የምረጡኝ ዘመቻዎች እንዲቋረጡ ስለማድረጋቸዉ 2 ክስተቶችን ሪፖርት ያደረጉ ሲሆን በአንደኛዉየምረጡን ዘመቻ አንዲት ዕጩ ተወዳዳሪ እያደረገች ነበረዉን የምረጡኝ ዘመቻ ለጊዚያዊነትም ቢሆን እንዲስተጓጎልባት ተደርጓል፡፡ በሁለተኛዉ ክስተት ወቅት የፀጥታ አካላት ወንድ እና ሴት የፖለቲካ ፓርቲ አባላት (ደጋፊዎች) የሚያደርጉት የምርጫ ቅስቀሳ እንዲስተጓጎል አድርገዋል፡፡

የኢ.ህ.ባ.ሴ.ማ ታዛቢዎች ሴቶች በመራጮች ትምህርት እና በምርጫ ዘመቻ ዝግጅቶች ላይ እንዳይሳተፉ የተደረጉ 8 ክስተቶችን መዝግበዋል፡፡ የጥቃቱ ሰለባዎች ሴት መራጮች ፣ ሴት እጩ ተመራጮች (6) እና የፖለቲካ ፓርቲ አባላት ወይም ደጋፊዎች

(2) ያካትታል፡፡ ጥቃት ፈፃሚዎች ባል/ሚስት (2) ፣ የፓርቲ አባላት ወይም ደጋፊዎች እና መራጮችን ሚመዘግብ ግለሰብ (1) ያካትታል፡፡ እነዚህ ክስተቶች በአብዛሃኛዉ የተመዘገቡት በአማራ ክልል ሲሆን በቤንሻንጉል ክልል እና ኦሮሚያ ክልሎችም ጥቂት ክስተቶች ተመዝግበዋል፡፡

የኢ.ህ.ባ.ሴ.ማ ታዛቢዎች በሴት እጩ ተወዳደሪዎች ላይ የተሰነዘሩ ወሲባዊ ይዘት ያለቸዉ እና የጥላቻ ንግግር የሚመስሉ 2 ድርጊቶች መፈፀማቸዉን ታዝበዋል፡፡ ጥቃቱን ፈፃሚዎች የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮችን እና የማህበረሰቡ አካላት የተካተቱበት እንደሆነ ተመዝግቧል፡፡ ሁሉም ክስተቶች የተመዘገቡት በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ነበር፡፡

የኢ.ህ.ባ.ሴ.ማ ታዛቢዎች ሴቶች ከምርጫ ቅስቀሳ ዘመቻዎች ተሳትፎ የተከለከሉባቸዉን 8 ክስተቶች መዝግበዋል፡፡ የጥቃቱ ሰለባዎች ሴት መራጮች (3) ፣ ፖሊተካ ፓርቲ አባላት ወይም ደጋፊዎች (2) እና ለመምረጥ ሚመዘገቡ ሴቶች (3) ናቸዉ፡፡ ጥቃቱን ፈፃሚዎች ባል (1) ፣ የፖለቲካ ፓርቲ አባላት ወይም ደጋፊዎች (1) እና የምርጫ አስፈፃሚ አባላት (1) ያካትታል፡፡ እነዚህ ክስተቶች በብዛት የተመዘገቡት በአማራ እና ኦሮሚያ ክልሎች ሲሆን የተወሰኑት ደግሞ በጋምቤላ እና ቤንሻንጉል ክልሎች እንዲሁም በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ተመዝግበዋል፡፡

የኢ.ህ.ባ.ሴ.ማ ታዛቢዎች ፖለቲካ ፓርቲ አባላትና የአካባቢ አስተዳደር ተወካዮች የሴት መራጮችን ወይም ለመምረጥ የተመዘገቡ ሴቶችን ድምጽ በማባባል ለማግኘት የተደረጉ ሙከራዎችን የሚመለከት 10 ክስተቶችን መዝገበዋል፡፡

# አካታችነት እና የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ

የማህበሩ ታዛቢዎች በተጨማሪ የቅድመ ምርጫ አካባቢ አጠቃላይ አካታችነት እና የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ገምግመዋል፡፡ የረጅም ግዜ ታዛቢዎች (ከምርጫ በፊት ያለውን ከምርጫ ጋር የተያያዘ ሁኔታ የሚከታተሉ) በሀገሪቱ ዙሪያ 341 መጠይቆችን የሞሉ ሲሆን የሚከተሉትን ግኝቶች ለማግኘት ችለዋል፡፡ ለ143 ጊዜያት የማህበሩ ታዛቢዎች ለሴት መራጮች ስለተዘጋጁ የመራጭ ትምህርት ቁሳቁሶች ለመታዘብ /ለመስማት ችለዋል፡፡ እነዚህ ተግባራት በዋናነት በአዲስአበባ፣ አማራ፣ ድሬዳዋ እና ቤንሻንጉል ክልሎች በብዛት የተከናወኑ ሲሆን በጋምቤላ፣ሲዳማ እና ደቡብ ክልል የታዩት እጅግ በጥቂቱ ነበር፡፡ ለ39 ግዜያት ደግሞ የማህበሩ ተዛቢዎች አካል ጉዳተኞች ወደ ምርጫ አካባቢ ለመድረስ እና/ወይም በምርጫ አስፈጻሚዎች ስለተፈጸመባቸው ያልተገባ አያያዝ ያቀረቡትን አቤቱታዎች ለመታዘብ/ለመስማት ችለዋል፡፡እነዚህ ክስተቶች በብዛት ያጋጠሙት በአማራ እና በድሬዳዋ ነበር፡፡ በ302 ጊዜያት ደግሞ በማህበሩ ከምርጫ በፊት ያለውን የምርጫ ሁኔታ የሚከታተሉ ታዛቢዎች ይሄን የመሰሉ አቤቱታዎችን አልታዘቡም/አልሰሙም፡፡

ለ216 ግዜያት ደግሞ የማህበሩ ታዛቢዎች የማህበሩ ታዛቢዎች፣ ዕጩዎች ወይም የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች ሁልግዜ ወይም አንዳንድ ጊዜ በምርጫ ዘመቻ ዝግጅቶች ወቅት ለሴት መራጮች አስፈላጊ ስለሆኑ ጉዳዮች እንደተናገሩ ታዝበዋል፡፡ ቢሆንም በ 125 ክስተቶች የማህበሩ ከምርጫ በፊት ያለውን የምርጫ ሁኔታ የሚከታተሉ ታዛቢዎችእጩዎች ወይም ፖለቲካል ፓረቲ አባላት ወይም የምርጫ ዘመቻ ተወካዮች ሁልግዜ ወይም አንዳንድ ግዜ በምርጫ ዘመቻ ዝግጅቶች ወቅት ተናግረው ነበር፡፡

# በምርጫ ቀን (ወቅት) በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶች ክትትል

## የክትትል ዘዴዎች

የኢትዮጵያ ህግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር በድምፅ መስጫ እና የመዝጊያ ሂደቱ እንዲሁም በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ ስለሚፈጸሙ ጥቃቶች ለመከታተል በ139 የምርጫ ጣቢያዎች 130 ታዛቢዎችን አሰማርቶ ነበር፡፡ በምርጫ ሂደቱ በሰሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶችን ከመታዘብ ባለፈ የኢ.ህ.ባ.ሴ.ማ በምርጫዉ ወቅት የምርጫ አስፈፃሚዎች ፣ ታዛቢዎች እና የሚዲያ ተወካይ በመሆን ያደረጉትን ተሳትፎም ለክቷል፡፡ በተጨማሪም የኮቪድ-19 ወረርሽኝ መከላከል ድንጋጌዎችን አፈፃፀም እና የምርጫ ጣቢያዎቹ ለአካል ጉዳተኞች ያላቸዉን ተደራሽነት ገምግሟል፡፡

130 የኢ.ህ.ባ.ሴ.ማ ታዛቢዎች መጠይቆችን አጠናቀዉ በመሙላት ወደ ማህበሩ የመረጃ ቋት ልከዋል፡፡ ከነዚህ መካከል ከአዲስ አበባ 89 ፣ ከአፋር ክልል 17 ፣ ከአማራ ክልል 69 ፣ ከቤንሻንጉል ክልል 19 ፣ ከድሬዳዋ ከተማ አስተዳድር 34 ፣ ከጋምቤላ ክልል 25 ፣ ከኦሮሚያ ክልል 60 ፣ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ሕዝቦች 41 እና ከሲዳማ ክልል 15 ምልከታዎች ተመዝግበዋል፡፡

እየያንዳንዳቸዉ ታዛቢዎች ከ2 እከ 4 የምርጫ ጣቢያዎችን የጎበኙ ሲሆን ከጣበያ ጣቢያ በመንቀሳቀስ የክትትል ስራዎቻቸዉን አከናዉነዋል፡፡ ታዛቢዎቹ የምርጫ ሂደቱን ትክክለኝነት የታዘቡ ሲሆን ፤ በምርጫ ጣቢያዎቹ ዉስጥ እና ዉጪ በመሆን በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶችን ታዝበዋል፡፡ ምልከታ የተደረገባቸዉ 86% የሚሆኑ የምርጫ ጣቢያዎች በከተሞች ዉስጥ የሚገኙ ሲሆን 14% የሚሆኑት ደግሞ በገጠር የሚገኙ ነበሩ፡፡ ሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች በሚያስብል ደረጃ መደበኛ የሆኑ ጣቢያዎች ሲሁኑ 1 ወታደራዊ እና 3 የከፍተኛ ት/ት (ዩኒቨርሲቲ)[3] ምርጫ ጣቢዎችን ተመልክተዋል[3]፡፡

## ከምርጫ ጣቢያዎች ዉጪ ያለ ሁኔታ

የኢ.ህ.ባ.ሴ.ማ ታዛቢዎች ምልከታ ባደረጉባቸዉ 369 የምርጫ ጣቢያዎች 80% የሚሆኑት ታዛቢዎች ሰልፎችን ተመልክተዋል፡፡ በኢ.ህ.ባ.ሴ.ማ ታዛቢዎች ምልከታ ከተደረገባቸዉ ጣቢያዎች 58% በሚሆኑት ላይ ለመወንዶች እና ለሴቶች የተለዩ ሰልፎችን ያልተመለከቱ ሲሆን ይህም በሴቶች ላይ የሚደርስ ወሲባዊ ትንኮሳን እንደሚያባብስ ስጋት የሚጨምር ነዉ፡፡ በኢ.ህ.ባ.ሴ.ማ ታዛቢዎች የተመዘገቡ አንድ አንድ ትዝብቶች ሰልፍ ላይ የነበሩ ሴት መራጮች ላይ ፆታዊ ትንኮሳዎችን ያካትታሉ፡፡

37% የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ደግሞ ለወንድ እና ለሴት መራጮች የተለያዩ ሰልፎች የነበሯቸዉ ሲሆን በኢ.ህ.ባ.ሴ.ማ ታዛቢዎች ምልከታ ከተደረገባቸዉ 5% በሚሆኑት የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ምንም አይነት ሰልፍ አለመታዩትን ተመልክተዋል፡፡ በኢ.ህ.ባ.ሴ.ማ ታዛቢዎች ምልከታ በተደረገባቸዉ 65% በሚሆኑት ድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ዉጪ ላይ ፀትታ አስከባሪ አካላት ወይም የታተዉ ሃይሎች እንደነበሩ ታዝበዋል፡፡

## የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች ተደራሽነት

የኢ.ህ.ባ.ሴ.ማ ታዛቢዎች ምልከታ ባደረጉባቸዉ 369 የምርጫ ጣቢያዎች 79% በሚሆኑት የአካል ጉዳት ላለባቸዉ ወይም እንደልብ ለመንቀሳቀስ ለሚቸገሩ (ለምሳሌ፡- አረጋዊያን ፣ ሕፃናትን ለሚይዙ) መራጮች በቀላሉ መድረስ (መግባት) የሚችሉባቸዉ እንደነበሩ ታዝበዋል፡፡ 84% የሚሆኑት ደግሞ ለወንዶችም ሆነ ለሴቶች በቀላሉ መግባት የሚችሉባቸዉ ሆነዉ እንዳገኟች እና 12% የሚሆኑት ግን ለወንዶች ብቻ ቀላል የሚባሉ እንደነበሩ ለመታዘብ ችለዋል፡፡

[3] University polling stations were set up for students to vote at the university rather than being required to return to their home locations.

## በምርጫ ሂደት የነበረዉ የስርዓተ-ፆታ ሚዛናዊነት

የኢ.ህ.ባ.ሴ.ማ ታዛቢዎች በተሰማሩባቸዉ የድምፅ መስጫ ጣቢያዎች በሙሉ የነበሩ የምርጫ አስፈፃሚዎች (ሰራተኞች) የሴቶች ዉክልና ያነሰ ነበር፡፡ የኢ.ህ.ባ.ሴ.ማ ታዛቢዎች በጎበኟቸዉ 369 የምርጫ ጣቢያዎች 87% የሚሆኑት በወንድ ሊቀመናብርት የሚመሩ የነበሩ ሲሆን በ18% ብቻ ሴት ሊቀመንበሮች እንደተሳተፉ ታዝበዋል፡፡ በተጨማሪም ከ369 ጣቢያዎች ዉስጥ 9% በሚሆኑት አንድም የሴት አባል አልነበራቸዉም፡፡

በኢ.ህ.ባ.ሴ.ማ ታዛቢዎች ምልከታ ከተደረገባቸዉ 369 ጣቢያዎች ዉስጥ በ248 ጣቢያዎች አንዳንድ ሴት ታዛቢዎች የነበሩ ሲሆን በ117 ጣቢያዎች ደግሞ አንዳንድ ሴት የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች ፤ በ20 ጣቢያዎች ደግሞ አንዳንድ ሴት ጋዜጠኞች ነበሩ፡፡ በ39 ጣቢያዎች  የሴት ባለድርሻ አካላት ዉክልና እንዳልነበረ ታዝበዋል፡፡

## ለኮቪድ-19 ድንጋጌዎች የነበረ ተገዥነት

በማህበሩ ከተጎበኙት 369 የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች 77% በሚሆኑት ሁሉም የምርጫ አስፈጻሚዎች ሁልጊዜ የአፍ እና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭምብል የለበሱ ሲሆን 19% በሚሆኑት ጣቢያዎች አንዳንድ የምርጫ አስፈጻሚ ሰራተኛ የአፍ እና የአፍንጫ መሸፈኛ ጭምብል ለብሰው ነበር፡፡

## ሴት መራጮች የመምረጥ መብታቸውን ያጡባቸው ክስተቶች

በማህበሩ ጉብኝት ከተደረገባቸው 369 ጣቢያዎች መካከል 7% በሚሆኑት ከ1-10 ሴት መራጮች በመራጮች ዝርዝር ውስጥ ባለማግኘታቸው እንዲመርጡ አልተፈቀደላቸውም ነበር፡፡ ይህም ምንም እንኳን ብቁ ባይሆኑም በሴት መራጮች መሆን በሚችሉ ሴቶች የነበረ የመምረጥ ፍላጎትን ይጠቁማል፡፡ከምርጫ ጣቢያዎች 7% በሚሆኑት ደግሞ ከ1-10 ሴት መራጮች በሌላ ምክንያቶች የተነሳ እንዲመርጡ አልተፈቀደላቸውም ነበር፡፡

ከ369 የምርጫ ጣቢያዎች 16% የሚሆኑት ከ1-10 ሴት መራጮች ምንም እገዛ የማያስፈልጋቸው ቢመስሉም እንዲመርጡ እገዛ ተደርጎላቸዋል፡፡

## በምርጫ ሂደት ወቅት በሴት መራጮች ላይ የተፈጸመ ጥቃት

ሁለት ታዛቢዎች በምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ በሴት መራጮች ላይ አካላዊ የሆነ ጥቃት ሲፈጸም ተመልክተዋል፡፡ ሴት መራጮች ከምርጫ ጣቢያ ግቢዎች እንዲወጡ ሲደረጉ ተመልክተዋል፡፡ ጥቃት ፈጻሚዎቹ የምርጫ አስፈጻሚ አባል እና ድምጽ ሰጪ ነበሩ፡፡ ሁሉም ክስተቶች ሪፖርት የተደረጉት ከድሬዳዋ ነበር፡፡

2 የወሲባዊ ትንኮሳ (የቃል እና አካላዊ) ክስተቶች ከምርጫ ጣቢያዎች ውጪ በማህበሩ ታዛቢዎች ሪፖርት ተደርገው ነበር፡፡ የወንድ መራጮች  በሰልፍ ላይ እያሉ ሴት መራጮችም በአካል ሲያዙ እና ሲነኩ ነበር፡፡ እነዚህ በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የተፈጸሙ ጥቃቶች ሪፖርት የተደረጉት ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ነበር፡፡

በምርጫ ቀን በማህበሩ ታዛቢዎች በሴቶች ላይ ስለደረሱ 9 የስነ-ልቦና ጥቃቶች ሪፖርት ተደርጎ ነበር፡፡ ጥቃት ፈጻሚዎች የፓርቲ ወኪሎች (1)፣ መራጮች (2) እና የምርጫ አስፈጻሚዎች (4) ያካትታሉ፡፡ እነዚህ በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የተፈጸሙ ጥቃቶች ሪፖርት የተደረጉት በአማራ ክልል፣በድሬዳዋ ከተማ፣ቤንሻንጉል እና አዲስአበባ ከተማ ነበር፡፡

## ሌሎች

97% ለሚሆኑት ጣቢያዎች ከከባድ የአየር ሁኔታዎች ወይም ሌላ የአየር ሁኔታዎች የተነሳ መራጮች ድምጽ ሳይሰጡ አልተመለሱም፡፡

## ምርጫን ማጠናቀቅ እና ቆጠራ

ከረጃጅም ሰልፎች የተነሳ የኢትዮጲያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ የምርጫ ማጠናቀቂያ ግዜ 12 ሰዓት መሆኑ ቀርቶ እስከ ምሽቱ 3 ሰዓት ድረስ ለ3 ሰዓታት በሀገሪቱ ዙሪያ እንዲራዘም አድርጎ ነበር፡፡ ምርጫን ማጠናቀቅና ቆጠራ የምርጫ መታዘብ እጅግ በጣም አስፈላጊ ከሆኑ ክፍሎች ውስጥ አንደኛው ነው፡፡

በምርጫ ጣቢያ ሰራተኞች እና ሌሎች የምርጫ ባለድርሻ አካላት የሴቶች ውክልና መጠን አነስተኛ በመሆኑ እና በደህንነት ዋስትና እጦት የተነሳ የማህበሩ የሴት ታዛቢዎች የምርጫ ጣቢያዎችን የድምጽ አሰጣጥ እና ቆጠራ ከመጠናቀቁ በፊት ቀድመው እንዲወጡ አድርጓል[4]፡፡

12 ሰዓት የድምጽ መስጫ ማስጠንቀቂያ ግዜ በተለይም የምርጫ ጣቢያ አስፈፃሚዎች ወንዶች ብቻ በሆኑባቸው ጣቢያዎች ለሴት የምርጫ ባለድርሻ አካላት ደህንነት አመቺ አልነበሩም። የቤተሰብ አባሎች ብዙ ግዜ ሴቶችን ከመሽ በኋላ ከቤት ውጪ እንዲቆዩ አይፈቅዱላቸውም። ከማህበሩ የሴት ታዛቢዎች ወሰጥ 12ቱ የድምፅ አሰጣጡ እና ቆጠራው እስከሚጠናቀቅ ድረስ በምርጫ ጣቢያ መቆየት አልቻሉም ነበር። ምክንያቱም የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ የድምፅ አሰጣጡን እስከ ሶስት ሰዓት ድረስ እንዲራዘም በመወሰኑ ነበር። ይህ ውሳኔ በምርጫ ሂደት ወቅት በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን በተለያዩ የሴት የምርጫ ባለድርሻ አካላት ላይ የምርጫ አስፈፃሚ አባላትን፣ ታዛቢዎችን፣ የፓርቲ የምርጫ ታዛቢዎችን እና የሚዲያ ተወካዮችን ሊደርስባቸው የሚችል ጥቃትን ጨምሯል።

## የማህበሩ ታዛቢዎች ምርጫውን ለመታዘብ ያላቸው መብቶች

ከ130 የማህበሩ ታዛቢዎች ውስጥ ሶስቱ በማለዳ ወደ ምርጫ ጣቢያዎች ለመግባት ችግር አጋጥሟቸው ነበር። እነሱም ምርጫውን ለመታዘብ ያላቸው መብት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ወደ ምርጫ ጣቢያ እንዳይገቡ በከለከሏቸው ግዜ የክትትል ዝርዝር እና የሞባይል ስልኮቻቸውን ትተው እንዲወጡ ባስገደዷቸው የምርጫ አስፈፃሚ ባለስልጣናት ተጥሶ ነበር። በተጨማሪ አንድ የማህብሩ ታዛቢ በድሬዳዋ ከሌሎች ታዛቢዎችና ጋዜጠኞች ጋር በሰኔ 15/2013 ዓ.ም እስከ ምሽቱ 1:00 ድረስ የምርጫ ጣቢያ ለቃ ለመውጣት አልተፈቀደላትም ነበር። እነርሱም ያለምንም ምግበ እና ውሀ ተይዘው እንዲቆዩ ተደርገው ነበር። በተጨማሪም ታዛቢዋ የፀጥታ አካል አብሯት ካልሆን በቀር ወደ መፀዳጃ ቤት እንድትሄድ አልተፈቀደላትም ነበር።

### በምርጫ ቀን የተፈጠሩ በምርጫ ሂደት ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶች አሳሳቢ ክስተቶች

ለ4 ግዜ የማህበሩ ታዛቢዎች የሴት ድምፅ ሰጪዎች እርዳታ የሚያስፍልጋቸው በማይመስሉበት ሁኔታ በምርጫ አስፈጻሚዎች እገዛ እንደተደረገላቸው ታዝበዋል። እነዚህ ክስተቶቸ ሪፖርት የተደረጉት በድሬደዋ፣ በቤንሻንጉል ጉምዝ እና በአማራ ክልል ነበር።

[4]In some cases, counting was not completed until the following day

3 ታዛቢዎች ሪፖርት እንዳደረጉት ደግሞ ብቁ ያልሆኑ ወንዶች እንዲመርጡ የተፈቀደላቸው ሲሆን 2 ታዛቢዎች ሪፖርት እንዳደረጉት ደግሞ ብቁ ያልነበሩ ሴት መራጮች ዝርዝር ላይ ስማቸው ባይገኝም ድምጽ እንዲሰጡ ተፈቅዶላቸው ነበር። እነዚህ ሁሉ የተመዘገቡ ምልከታዎች ሪፖርት የተደረጉት በጋምቤላ ውስጥ ነበር።

በማህበሩ ክትትል ከተደረገባቸው 369 የምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ በአምስቱ ጣቢያ ያልተፈቀደላቸው ግለሰቦች ተገኝተው ነበር። እነዚህ ክስተቶች ሪፖርት የተደረጉት በአዲስ አበባ፣ ጋምቤላ እና ኦሮሚያ ነበር። ማህበሩ ክትትል ካደረገባቸው 369 ጣቢያዎች መካከል 17ቱ ጣቢያዎች የድምጽ መስጫ ወረቀት እጥረት ተከስቶ ነበር። ይህ ደግሞ ሴቶች በተለይም በቤት ውስጥ ካለባቸው ሀላፊነቶች ጾታ ተኮር ከሆኑ አመለካከቶች የተነሳ ድምጻቸውን እንዳይሰጡ ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ተጽእኖ አሳድሮባቸው ነበር። እነዚህ የጠፉ የድምጽ መስጫ ካርዶች በሲዳማ(9)፣ በጋምቤላ(3)፣ በቤንሻንጉል(3) እና በአዲስ አበባ(2) ነበሩ።

የማህበሩ ታዛቢዎች በጎበኙዋቸው 3 የምርጫ ጣቢያዎች ደግሞ ምርጫ እንደተሰረዘና በእነዚያ ድምጽ መስጫ ክልሎች እንደማይከናወን ለመገንዘብ ችለዋል።

3 የማህበሩ ታዛቢዎች ምርጫውን እንዲታዘቡ አልተፈቀደላቸውም ወይም የመታዘብ ስራቸው እንዲስተጓጎል\እንዲቋረጥ ተደርጎ ነበር። አንድ ታዛቢ ደግሞ ምንም እንኳን የፍቃድ ካርድ ቢኖራትም በመታወቂያዋ ልይ ፎቶ ባለመኖሩ የተነሳ አልተፈቀደላትም ነበር። አንድ ታዛቢ ደግሞ የምርጫ ጣቢያ ለቃ እንድትወጣና በውጪ የክትትል ስራን እንድታከናውን አልተፈቀደላትም ነበር። አንድ ታዛቢ ደግሞ በምርጫ ጣቢያ ውስጥ የክትትል መጠይቆችንና ስልክ እንድትጠቀም አልተፈቀደም ነበር። እነዚህ ክስተቶች የተፈጸሙት አዲስ አበባ፣ ድሬደዋ እና ኦሮሚያ ነበር።

በማህበሩ ጉብኝት ከተደረገባችው 369 ጣቢያዎች ውስጥ በ5ቱ የምርጫ ጣቢያዎች ሴቶች ለመምረጥ መተው የነበረ ቢሆንም በመራጮች ዝርዝር ውስጥ ግን አልነበሩም። እነዚህ ክስተቶች ሪፖርት የተደረጉት በድሬደዋ እና በአማራ ክልል ነበር።

## ምክረ-ሃሳቦች

ከላይ በቀረቡት ግኝቶች መሰረት ማህበሩ የሚከተሉትን የመጀመሪያ ደረጃ የመፍትሄ ሀሳቦችን ቁልፍ የሆኑ ባለድርሻ አካላት ላይ በማተኮር ይሰጣል።

### ለኢትዮጲያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ

- በኢትዮጲያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ውስጥም ሆነ ውጪ ምንም አይነት መልክ ያለው በሴቶች ላይ የሚፈጸም ጥቃትን መከልከልን ጨምሮ ጥቃቶች ሲፈጸሙ የሚከተሉ ቅጣቶችን ማብራራት፣ ሚስጥር በተጠበቀ ሁኔታ የሪፖርት ማድረጊያ ሰንሰለቶችን መፍጠርና እነዚህን ድንጋጌዎች እንዲፈጸሙ ማስደረግ
- ወሲባዊ ይዘት ያላቸውን አዋራጅ የሆኑ የቋንቋ አጠቃቀሞችን በሴት እጩዎች፣ ድምጽ ሰጪዎች፣ ታዛቢዎች፣ የምርጫ ጣቢያ ሰራተኞችና የተመረጡ ሴቶች ላይ በጥቅም ላይ እንዳይውሉ የሚከለክሉ ህጎች\ድንጋጌዎች መተግበራቸውን ማረጋገጥ
- በኢትዮጲያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ፖለቲካ ፓርቲዎች አስገዳጅ የሆነ የስነ-ጾታ ምጥጥን እንዲኖርና መመረጥ ያለባቸውን የሴት አባላት ዝቅተኛ ቁጥር እንዲኖር ያለውን ቁርጠኝነት እንዲፈጽም ማስገደድ
- በኢትዮጲያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የስነ-ጾታ ክፍል ሚናዎቹንና ሀላፊነቶቹን ለመወጣት የሚያስችሉ ሀብቶችና ስልጣን ያለው መሆኑን ማረጋገጥ
- የምርጫ አስፈጻሚዎችንና የጣቢያ የጸጥታ አካላትን ስለ ስነ-ጾታ እኩልነት፣ በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን ለመቀነስ የሚያስችሉ አሰራሮችን ማስቀመጥ።
- በመራጮች ትምህርት ውስጥ የምርጫ ካርድ ሚስጥራዊነት አስፈላጊነትን በመመልከት ንቃት ህሊና ከፍ ማድረግን ጨምሮ በምርጫ ውቅት በሴቶች ላይ ስለሚፈጸሙ ጥቃቶች ጽንሰ ሃሳብን ማካተት
- የኢትዮጲያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በምርጫ ሂደት የሴቶችን እኩልነትና ተሳትፎ ከፍ ለማድረግ ላለው ቁርጠኝነት መወሰድ ስላለባቸው ግልጽ እርምጃዎች ንቃተ ህሊናን ከፍ ማድረግ
- ለኢትዮጲያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ስታፍ አባላትና ባለድርሻ አካላት በምርጫ ሂደት ወቅት በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶች በሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ላይ ስለሚያሳድሩት ተጽእኖ እና የምርጫን ዲሞክራሲያዊ ሂደት ጥራት በማሳነሱ ላይ የሚያተኩሩ ለስነ-ጾታ ጉዳዮች ጥንቃቄ የማድረግ ስልጣንን መተግበር
- ከምርጫ በፊት ተንቅሳቃሽ የምዝገባ ቡድንን ሴቶችን ያካተተ በማሰማራት በተለይም በገጠር አካባቢዎች የመራጭ ሴቶችን ምዝገባ የማሳለጥ ስራ ማከናወን
- ለታዛቢዎች የእዉቅና ፈቃድ (ባጅ) በጊዜ እንዲሰጥ ማድረግና በምርጫ የጊዜ ሰሌዳ ላይ የሚደረጉ ለዉጦችን ለህዝቡ በጊዜ ማሳወቅ፡፡

### ለኢትዮጵያ መንግስት

- በምርጫ ሂደት ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶችን በመመርመር እና በዳኝነት ስራ ላይ ለተሰማሩ ህግ አስፈፃሚ አካላት ፣ ለፖሊስ ፣ ለህግ አስከባሪ አካላት ስነ-ፆታ ተኮር የሆነ ስልጠናን እንዲያገኙ ማድረግ

- ሴት የምርጫ አስፈፃሚ/አስተባባሪ ሰራተኞችን ደህንነት ለመጠበቅ ይረዳ ዘንድ የሴት ፀጥታ አስከባሪ አካላትን ቁጥር ከፍ ማድረግ
- በሴቶች ላይ ሚፈፀሙ ወሲባዊ ትንኮሳዎችን ለመከላከል የሚያስችሉ የህግ ለዉጦችን ማድረግ
- ህግ አስከባሪ አካላት በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ የጥቃት ወንጀሎችን በህግ ፊት ለማቅረብ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጋር በመተባበር በቅርበት እንዲሰሩ ማበረታታት፡፡

## ለሲቪክ ማህበራት ድርጅቶች

- ከተመረጡ አሰራሮች ጋር በተጣጣመ መልኩ ስነ-ፆታ ተኮር የሆኑ እና ለስነ-ፆታዊ ጉዳዮች ምላሽ የሚሰጥ የምርጫ መታዘብ ስራዎችን ማከናወን እንዲቀጥሉ
- የሴቶችን ፖለቲካዊ ተሳትፎ ሚና የሚያሳዩ እና በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶችን አስመልክቶ ግንዛቤ የማስፋፋት ዘመቻዎችን እንዲደግፉ
- በምርጫ ሂደቶች ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶችን ለመቀነስ ይረዳ ዘንድ ምርጫ አስፈፃሚዎችን (ሰራተኞችን) ፣ ፖሊስ ፣ ህግ አስከባሪ እና አስፈፃሚ አካላትን ማሰልጠን
- በምርጫ ሂደቶች በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ የሃይል እርምጃዎችን ለመታገል በሴት አመራሮች መካከል የአንድነት ትስስሮችን ማሳደግ የሚያስችሉ መድረኮችን መፍጠር
- ሴቶች በምርጫ ሂደቶች ሙሉ በሙሉ እና በእኩልነት ለመሳተፍ የሚያስችላቸዉን ህጎችና ፖሊሲዎች ለማሻሻል ያለሙ የሙጎታ/ግፊት የመፍጠር ስራዎችን መስራት

## ለፖለቲካ ፓርቲዎች

- የሴቶች በብት እንዲከበር የሚያስችሉ የስነ-ምግባር ህጎችንና የድርጊት መርሃ-ግብሮችን ማጎልበት እና ማስፈፀም ፤ እንዲሁም ወሲባዊ ጥቃቶችን መቅረፍ የሚያስችሉ የማይታገሱ ፖሊሲዎችን ማዉጣት
- ለፖለቲካ ፓርቲ አባላትና ለፓርቲ የምርጫ ታዛቢዎች የግድ ሊወስዱት የሚገባቸዉን የስነ-ፆታ ስልጠናና ትምህርቶችን መስጠት
- ስለ ስነ-ፆታ እኩልነትና በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ ስለሚፈፀሙ ጥቃቶች የፓርቲ የዉስጥ መተዳደሪያ ደንብና አሰራሮችን መቆጣጠር እና ማስፈፀም
- የተመረጡት ሴት ባለሥልጣናትን ቁጥር የሚያስገድድ አስገዳጅ የሥርዓተ-ፆታ ኮታ እንዲቀበሉ
- መመረጥ ያለባቸዉን የሴት ተመራጮች ዝቅተኛ ቁጥር በሚመለከት አስገዳጅ የሆነ የስርዓተ-ፆታ ኮታዎች መተግበር

## ለመገናኛ ብዙሃን (ሚዲያዎች)

- የስርዓተ-ፆታ እኩልነት አለመኖርና ስነ-ፆታን በሚመለከት ያሉ የተሳሳቱ አመለካከቶች (አድሎአዊነትን) በሚመለከት በሚያቀርቡት የዘገባ ይዘት ትምህርትን መስጠት
- በስነ-ፆታ እኩልነትና በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ ስለሚፈፀሙ ጥቃቶች ለሚዲያ ሰራተኞች የአቅም ግንባታ ስራን ማከናወን
- በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ ስለሚፈፀሙ ጥቃቶች በተለያየ መልኩ ማዉራት የሚያስችሉ መድረኮችን በመፍጠር የግንዛቤ ማስፋፊያ ስራዎችን መስራት
- ስለ ምርጫ ሂደቶች የሴቶችን ንቃተ ህሊናና መረዳት ከፍ ለማድረግ የሚያስችሉ መረጃዎችን በሚገባ መልኩ ማዘጋጀት እና ማሰራጨት

## ለአጋር ድርጅቶች (ለጋሽ ተቋማት)

- በመንግስት ፣ በምርጫ ቦርድ እና የሲቪክ ማህበራት አነሳሽነት በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ በሚፈፀሙ ጥቃቶች ዙሪያ ግንዛቤ ለመፍጠር የሚጀመሩ እንቅስቃሴዎችን መደገፍ

- በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ በሚፈፀሙ ጥቃቶች እና በፆታዊ እኩልነት ዙሪያ የባለድርሻ አካላትን አቅም ለማጎልበት እገዛ ማድረግ
- በፆታ ተኮር እና ስነ-ፆታዊ ምልከታዎች ላይ የሃገር በቀል የሲቪክ ማህበራት ድርጅቶችን ጥረት መደገፍ

## ማጠቃለያ

የኢትዮጵያ ህግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር በቅድመ-ምርጫ እና በምርጫ ቀን በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶችን በሚመለከት ባደረገዉ ምልከታ የመዘገባቸዉን ግኝቶች እና የሚጠበቅበትን ምክረ-ሃሰሳቦች ትንታኔ ያካተተ ሰፊ ሪፖርት ወደፊት ያቀርባል፡ ፡ ይህ እንዲሆን ያደረጉትን የማህበሩ ታዛቢዎች ፤ የክልል ቢሮ ተወካዮች እና በተፈጠረዉ ትስስር በዚህ እጅግ አስፈላጊ ጥረታችን ላይ የተሳተፉትን ሁሉ የኢ.ህ.ባ.ሴ.ማ ያመሰግናል፡፡

## ስለ እኛ

የኢትዮጵያ ሕግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር በፌደራል ደረጃ በ1987 ዓ.ም የተቋቋመ ፤ በበጎ አድራጎት ማህበራትና ድርጅቶች ኤጀንሲ የተመዘገበ የሲቪክ ማህበር ሲሆን ላለፉት ከ25 ዓመታት በላይ የሴቶችን ማህበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ ፣ ፖለቲካዊ እና ሕጋዊ መብቶች እንዲታወቁ በማድረግ ሴቶች በሕገ-መንግስቱ እና በሌሎች ሕጎች በተመላከቱ መብቶቻቸዉ እንዲጠቀሙ የሚያግዙ ስራዎችን ሲሰራ ቆይቷል ፡፡

የማህበሩ ግብ ሴቶች በሁለንተናዊ ዘርፍ እኩል ተጠቃሚና ተሳታፊ እንዲሆኑ አስተዋፅኦ ማድረግ ሲሆን በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ፆታዊ ጥቃቶችን መከላከልና ለሴቶች ከጥቃት የፀዳ ከባቢን መፍጠርን አላማዉ አድርጎ የተለያዩ ስልቶችን በመንደፍ በዋና ፅ/ቤቱ አዲስ አበባ እና በ8 የክልል ከተሞች ማለትም በአዳማ ፣ በሐዋሳ ፣ በባህር ዳር ፣ በድሬ ዳዋ ፣ በጋምቤላ ፣ በአሶሳ ፣ በጅግጅጋ እና ሰመራ በሚገኙት ቅርንጫፍ ጽ/ ቤቶቹ በመስራት ላይ ይገኛል፡፡

የማህበሩ አገልግሎት ለሁሉም ተደራሽ እንዲሆን ከማድረግ አንፃር ማህበሩ ባሉት የክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ ስር በሚገኙ ዞን እና ወረዳዎች ላይ ከማህበረሰቡ በተዉጣጡ በጎ ፈቃደኞች አማካኝነት የሚሰጠዉ አገልግሎት እንዲቀጥል እየሰራ ሲሆን እስከአሁን ድረስም በሃገሪቱ በአጠቃላይ 54 በጎ ፈቃደኛ ኮሚቴ ማዕከሎችን አቋቁሟል፡፡

ከነዚህ አማራጮች በተጨማሪ በተለይ ማህበሩ በጉልህ የሚታወቅበትን ነፃ የህግ ድጋፍ አገልግሎት በመላ ሃገሪቱ ለሚገኙና ድጋፍ ለሚሹ ሴቶች ለማዳረስ ይረዳ ዘንድ ነፃ የስልክ ጥሪ ማዕከል/Hotline servise በማቋቋም በ7711 አጭር የነፃ ስልክ መስመር አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡

## ስለ “በምርጫ ሂደቶች ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቶች” ፕሮጀክት

የኢትዮጵያ ሕግ ባለሙያ ሴቶች ማህበር ከናሽናል ዲሞክራቲክ ኢንስቲቲዉት (ኤን.ዲ.አይ) ጋር ባደረጉት የአጋርነት ስምምነት እና ከዩናይትድስቴት ኤጀንሲ ፎር ኢንተርናሽናል ዲቨሎፕመንት (ዩ.ኤስ.ኤ.አይ.ዲ) በተገኘ የገንዘብ እና የቴክኒክ ድጋፍ ስር “በምርጫ ወቅት በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ ጥቃቃች” በሚል ፕርጀክት ነድፎ እየሰራ ይገኛል፡፡ የፕሮጀክቱ ዋና አላማ በቅድመ-ምርጫ ወቅት እና በምርጫ ቀን ምልከታዎችን (የመታዘብ ስራዎችን) ለማድረግ እንዲሁም በነፃ የስልክ ጥሪ መስመር 7711 ከማህበረሰቡ ጥቆማዎች ለመቀበል ነዉ፡፡ የምልከታ ግኝቶችን እና በነፃ ጥሪ ማዕከሉ የሚመዘገቡ ግኝቶች ማህበሩ ወደፊት በዘርፉ ለሚያደርጋቸዉ የግፊት (የሙግታ) ስራዎች ግብዓት የሚሆኑ ይሆናል፡፡